Calgary

# Vehicle for Hire

**ማስታወቂያ #003**

**አስቸኳይ ለውጦች - በፖሊስ የታክሲ ሹፌር መንጃ ፍቃድ ፍተሻዎች** **ኦክቶበር 1 2024**

---

ተሽከርካሪ ለኪራይ ለአዲስ የታክሲ መንጃ ፍቃድ ማመልከቻ እና ለእድሳት የታክሲ መንጃ ፍቃድ ማመልከቻዎች የሚደረግ የፖሊስ መረጃ ፍተሻ የማግኘት ሂደት ላይ ስላለው ጠቃሚ ለውጥ ሊያሳውቅዎ ይፈልጋል።

በአሁኑ ጊዜ የፖሊስ ፍተሻዎችን ለማመቻቸት የውስጥ ስርዓታችን ከካልጋሪ ፖሊስ አገልግሎት ጋር ተቀናጅቷል። ነገር ግን፣ የካልጋሪ ፖሊስ አገልግሎት **ከጃንዋሪ 1፣ 2025 ጀምሮ** ይህን ውህደት እንደማይደግፉ አሳውቀዋል። በመሆኑም **ሁሉም የታክሲ ሹፌር** አመልካቾች **በሚኖሩበት ከተማ የፖሊስ አገልግሎት የየራሳቸውን የፖሊስ ፍተሻ በቀጥታ ወስደው** ውጤታቸውን ተሽከርካሪ ለኪራይ ቢሮ እንደ አዲስ ወይም እድሳት ማመልከቻ ማስገባት ይጠበቅባቸዋል።

ለዚህ ሽግግር ለመዘጋጀት እስከ ጃንዋሪ 1፣ 2025 ድረስ ሁለቱንም ያካተተ የተቀናጀ አካሄድ ይኖረናል። በዚህ ጊዜ የፖሊስ ፍተሻዎችን አሁን ባለን ስርዓት ማመቻቸት እንቀጥላለን፣ ነገር ግን አመልካቾች ህጋዊ የሆነ የፖሊስ ፍተሻ በእኛ የቢሮ ተቀባይ የማቅረብ አማራጭ አላቸው። ከጃንዋሪ 1፣ 2025 ጀምሮ የታክሲ መንጃ ፈቃዳቸውን ለማመልከት ወይም ለማደስ የሚፈልጉ አሽከርካሪዎች የራሳቸውን የፖሊስ ፍተሻ ወደ ተሽከርካሪ ለኪራይ ቢሮ ማስገባት አለባቸው። የፖሊስ ፍተሻዎቹ የሚገቡት ማመልከቻው ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ባሉት 60 ቀናት ውስጥ መሆን አለበት።

የዚህ ለውጥ ጥቅም - በአሁኑ ጊዜ ለሁለቱም የታክሲ መንጃ ፍቃድ እና የትራንስፖርት ኔትወርክ መንጃ ፍቃድ የሚያመለክቱ ግለሰቦች ሁለት የተለያዩ የፖሊስ ፍተሻዎችን ማግኘት አለባቸው። በአዲሱ ሂደት የአመልካቾችን ጊዜ በመቆጠብ እና ወጪን በመቀነስ አንድ የፖሊስ ፍተሻ ለሁለቱም ማመልከቻዎች ተቀባይነት ይኖረዋል።

ለካልጋሪ ፖሊስ ፍተሻ ለማመልከት እባክዎ ይህን ሊንክ ይከተሉ፡- *calgarypolicechecks*

ማንኛቸውም ጥያቄዎች ካሉዎት፣ እባክዎን ለ vfhlicensing@calgary.ca ኢሜይል ያድርጉ።

ከሰላምታ ጋር፣

ኮሪይ ፖርተር
ምክትል ኃላፊ፣ ተሽከርካሪ ለኪራይ
የህዝብ ተሽከርካሪ ደረጃዎች